ጥበብን ማወቅ ምሳሌ፡1፡1-9

መግቢያ፡- ከ3000 ዓመታት በፊት እግዚአብሔር ለሰሎሞን ጥበብን ሰጠው፡፡ ነገር ግን በምሳሌ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ ምሳሌዎች ዛሬም ለእኛ የሚያስፈልጉ እውነቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ምሳሌዎች አጠቃላይ ሕጎች ሲሆኑ በሕይወታችን ማድረግ ያለብንን ነገር መወሰን እንድንችል ይረዱናል፡፡ ምሳሌዎች ሕይወትን በእግዚአብሔር መንገድ መምራት የምንችልበትን ጥበብ ይሰጡናል፡፡

ምሳሌ፡1፡1-9 አንብብ

1. መጽሐፈ ምሳሌን የጻፈው ማንነው?
2. ለማንነው የጻፈው?
3. ለምንድነው የጻፈው?
4. የጥበብ መጀመሪያ ምንድነው? ለምን?
5. ከቁጥር 1-6 ያለውን በጥንቃቄ አንብብና ከዚህ ክፍል የምናገኘውን እውነት ተወያይ፡፡
6. የእያንዳንዱ ቤተሰብ ልጆች እንዴት መኖር እንዳለባቸው ማስተማር ያለበት ማንነው? አንተ ይህን ለቤተሰብህ ወይም ለጓደኞችህ እንዴት ታስተምራለህ?
7. ጥበብ እንዲሰጥህ ትፈልጋለህ? ጥበብን ለመማር በዚህ ሣምንት ማድረግ ያለብህ ምንድነው?